# አዲሱ የደቡብ ኢትዮጵያ የክላስተር አደረጃጀትና የሀብት ክፍፍል ተግዳሮቶች፡ የዘይሴ-ጋሞ እና ቀቤና-ጉራጌ ድንበር አካባቢ ግጭቶች

አሰበ ረጋሳ ደበሎ እና ያዕቆብ ጨቃ ሒዶቶ

## ማጠቃለያ


ይህ ሪፖርት በደቡብ ኢትዮጵያ ከ2010 ጀምሮ የተተገበረውን የአስተዳደር ክላስተር መልሶ ማዋቀር ተከትሎ፣ በዘይሴ እና በጋሞ እንዲሁም በቀቤና እና በጉራጌ ብሔረሰቦች መካከል በተከሰቱ ውጥረቶች ላይ ያተኩራል። ከ2010 ጀምሮ ከድንበር ይገባኛል እና ራስን በራስ ከማስተዳደር ጥያቄዎች ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶች በኢትዮጵያ እየጨመሩ መጥተዋል። ሆኖም የሚከሰቱ የሰላምና የፀጥታ ችግሮችን ለመፍታት፤ ብልጽግና ፓርቲ በቀድሞው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት ውስጥ የክልል እና የአካባቢ አስተዳደሮችን በአዲስ መልክ አዋቅሯል።

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በብዝሃነት፣ በሰፊ የፖለቲካዊ ብዝኃነት፣ ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ እና አንድነትን ለማስፈን በሚደረገው ጥረት ምክንያት የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ፌዴሬሽን ትንሽ ማሳያ ነበር ተብሎ ሊወሰድ ይችላል። በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የተከሰተው አለመረጋጋት ራስን በራስ ከማስተዳደር ጥያቄዎች ጋር ተያይዞ የመጣ ሲሆን፣ በ2011 መንግሥት የሲዳማን የረዥም ጊዜ የክልልነት ጥያቄ ከተቀበለ በኋላ ተባብሷል። ይህንን ተከትሎ በሌሎች 12 ዞኖችም ተመሳሳይ ራስን በራስ የማስተዳደር ንቅናቄዎች ታይተዋል። ይህም በደቡብ ክልል ውስጥ ለረጅም ጊዜ የቆዩና ሥር የሰደዱ ራስን በራስ የማስተዳደር እና የድንበር ውዝግቦችን ለመፍታት፣ እንዲሁም ለማንነት ጥያቄዎች ዕውቅና መስጠትን አስፈላጊ አድርጎታል።

ይህ ጥናት ከ2010 በኋላ ከተደረገው የክልልነት መዋቅር ማሻሻያና ድንበር ማካለል ጋር በተገናኘ የታዩ የሰላም እና የግጭት ሁኔታዎችን አንድምታ ለመረዳት ያለመ ሲሆን፣ ሁለት አስረጂ የጥናት ናሙናዎች ላይ ያተኩራል። የመጀመሪያው በጋሞ ዞን የዘይሴ ተወላጆች በሚኖሩባቸው አካባቢዎች የተፈጠረውን ሁከት የሚመለከት

ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የወልቂጤ ከተማ እና የቀቤና ልዩ ወረዳ መካከል የተከሰቱት ግጭቶችና ውዝግቦችን ይመለከታል።

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት እና የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት በነሐሴ 2015 ከተመሰረቱ በኋላ፣ በእነዚህ ክልሎች ከላይ በተጠቀሱት ሁለት አካባቢዎች ግጭቶች ተከስተዋል። እነዚህ አዲስ ክልሎች ሲደራጁ በብሔሮች መካከል አለመግባባት እንዳይፈጠር የክልል ቢሮዎቻቸውን ወደ ተለያዩ ዞኖች የማከፋፈልና አዳዲስ የዞንና የልዩ ወረዳ የአስተዳደር መዋቅሮችን የመፍጠር ጥረት ተደርጓል። ሆኖም ግን፥ ከላይ የተጠቀሱትን ግጭቶች እንዳይከሰቱ አላደረጉም።፡

ከግጭቶቹ መንስዔዎች አንዱ በአስተዳደር መዋቅር ውስጥ የሚታየውና ከላይ ወደ ታች የሚተላለፍ አመራር መሆኑን ጥናቶቹ ያመለክታሉ። ይህ ሁኔታ ወሳኝ ለሆኑ ጉዳዮች ሰላማዊ የውይይት ዕድሎችን ባለመፍጠሩ ጉዳዩን አባብሶ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ግቦችን በአመፅ ማሳካትን አማራጭ ያደርጋል።

በተጨማሪም ድርድር፣ ምክክር እና ሌሎች ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን መጠቀም እያሽቆለቆለ ባለበት ነባራዊ ሁኔታ፣ የማኅበራዊ ትስስር መድረኮች ግጭትን በማባባስ በተፎካካሪ ወገኖች መካከል ያለውን ግንኙነት በይበልጥ እያሻከሩ ነው። ይህም በምላሹ በሰላም አብረው እየኖሩ የሚገኙ በርካታ ማኅበረሰቦችን የዕለት ተዕለት ኑሮ ያወሳስባል።

በቁጥር አናሳ የሆኑ ቡድኖችን መብት ለመጠበቅ እና በቁጥር በርካታ የሆኑ ቡድኖችን መድሎ ለመከላከል ያለመ ተቋማዊ አሠራር አለመኖሩ ግጭቶች እንዲቀጥሉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለውም ጥናቶች ያመለክታሉ።

በኢትዮጵያ የድንበር እና የማንነት ጥያቄዎች ትልቅ ስፍራ አላቸው። የማንነት እና የሀብት ጉዳዮች ከድንበር እና ከመሬት ጋር በእጅጉ የተሳሰሩ ናቸው። በመሆኑም ታሪካዊ እና ወቅታዊ የይገባኛል ጥያቄዎችን ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ እነዚህን ስፍራዎች በመቀየር ማዋቀር ቅሬታ እና አለመረጋጋትን ያስከትላል።

በድኅረ 1983 ኢትዮጵያ የተመሠረተውን ማንነትን መሠረት ያደረገ አስተዳደራዊ መዋቅርን እንደገና መልሶ ማዋቀር በሕገ መንግሥቱ ከተሰጡ ራስን በራስ የማስተዳደር መብቶች አንጻር ያልታሰበ ውጤት ሊኖረው ይችላል ። የደቡብ ኢትዮጵያ እና የመካከለኛው ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥታት ውስጥ ራስን በራስ ለማስተዳደር ከሚደረጉ ጥረቶች ጋር በተያያዥ እየተከሰቱ ያሉትን ችግሮች ለመቀነስ፤ የክልል እና የፌደራል መንግሥታት የዜጎችን መሠረታዊ መብቶችን ማስጠበቅ፣ በብሔሮች መካከል እኩልነትን ማስፈን እንዲሁም የክልል እና የአካባቢ ባለሥልጣናትን ተጠያቂነት የሚያረጋግጥ አሠራር ማስፈን ላይ ትኩረት አድርገው መሥራት ይኖርባቸዋል።

## የኢትዮጵያ የሰላም ምርምር ተቋም

ይህ ሪፖርት ለኢትዮጵያ የሰላም ምርምር ተቋም የተጻፈ ሲሆን፥ የድንበር ውዝግቦችን የተመለከቱ ጭብጦች የተዳሰሱበት የዕውቀት ለሰላም (Knowledge for Peace) ምርምሮች አካል ነው። የሰላም ምርምር ተቋም ገለልተኛ የሆነ ወቅታዊ የሰላምና የግጭት ትንታኔዎችን ከኢትዮጵያዊ ባለሙያዎችና ተመራማሪዎች በማቀናጀት በአገሪቱ ግጭት አገናዛቢ የሆነ የፖሊሲና ፕሮግራም ቀረጻ እንዲኖር ያግዛል። ተቋሙ በሪፍት ቫሊ ኢንስቲትዩት (አር ቪ አይ) የሚተዳደር ሲሆን፥ በእንግሊዝ መንግሥት ድጋፍ ይደረግለታል።

## የስምጥ ሸለቆ የጥናት ተቋም

የስምጥ ሸለቆ የጥናት ተቋም በምስራቅና ማዕከላዊ አፍሪካ የሚሠራ ሲሆን፣ አገር በቀል ዕውቀቶች በማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ላይ አስተዋጽኦ እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። የቅጂ መብት © የስምጥ ሸለቆ የጥናት ተቋም 2017። ይህ ሪፖርት በክሪኤቲቭ ኮመንስ አሠራር መሠረት ለንግድ ላልሆነ ዓላማ ይዘቱ ሳይቀየር መጠቀም እንዲቻል ተፈቅዶ የታተመ ነው (CC BY-NC-ND 4.0)።

Rift Valley Institute
MAKING LOCAL KNOWLEDGE WORK

Peace Research Facility